# የኬሚካል ይዘት

Standard

2021-06-22

**ይዘቶች**

1 **መግቢያ** ... 3

2 **ፍቺዎች** ... 3

3 **ሃላፊነቶች** ... 4

3.1 አስተዳዳሪዎች/ሃላፊነት ያለበት ሰው ... 4

3.2 ኬሚካል የሚይዙ ግለሰቦች ... 4

4 **መስፈርቶች** ... 4

4.1 ጠቅላላ መስፈርቶች ... 4

4.2 የደህንነት መረጃ ሉህ ... 5

4.3 ምልክት ማድረግ እና መለጠፍ ... 5

4.4 ተቀጣጣይ እና/ወይም ፈንጂ እቃዎች ... 5

5 **የህክምና አቋም እና ምላሽ** ... 5

6 **የተጋላጭነት ግምገማ እና እቅድ** ... 6

7 **ክትትል እና ግምገማ** ... 6

8 **ማጣቀሻዎች** ... 6

9 **የለውጥ መረጃ** ... 6

© Ericsson AB 2021

ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ሲሆን እናም ያለ ማስታወቂያ ሊለወጥ ይችላል። በእውነታ ትክክል አለመሆን ወይም በቶፖግራፊካል ስህተቶች ኤሪክሰን ምንም ሀላፊነት አይወስድም።

# 1 መግቢያ

በኤሪክሰን ቦታ ሆነው ሲሰሩ ደህንነቱን እና የአካባቢያዊ ንጽህናን በጠበቀ መልኩ ኬሚካሎችን መያዛቸውን ለማረገገጥ የሚወሰዱ እርምጃችን ይገልጻል። ይህ የሚከተሉትን ያካትታል፡

- በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ የሆነውን አማራጭ በመምረጥ በተቻለው ቦታ ሁሉ ኬሚካሎች አያያዝ ጋር በተያያዘ የሚመጡ ተጋላጭነቶችን ይቀንሱ።
- ኬሚካሎች አያያዝ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን ከተጋላጭነት ለመጠበቅ እና አከባቢውንም ለመጠበቅ ድንጋጌዎች መቅረባቸውን ማረጋገጥ።
- የቀረቡት ድንጋጌዎች የአከባቢውን ለኬሚካል አያያዝ ተፈጻሚነት ያለውን ህግ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- እንደ ተጋላጭነት ግምገማ አካል ከኬሚካሎች ጋር ከመስራት ጋር የተያያዙ ተጋላጭነቶች መለየትችቸው፣ መዳሰሳቸው እና በተገቢው ሁኔታ መተዳደራቸው(ለምሳሌ አደጋዎች፣ ተጋላጭነት) ማረጋገጥ።
- ለየግል መከላከያ መሰሪያ (PPE) መምጣት፣ ጥቅም ላይ መዋል እና ክምችት ድልደላዎችን ማቋቋም።
- ለአካባቢው መከላከያ መሰሪያ መምጣት፣ ጥቅም ላይ መዋል እና ክምችት ድልደላዎችን ማቋቋም።

የአከባቢ ህጎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ከሚፈለጉት በላይ በሚሆኑበት ቦታዎች የአከባቢው የሕግ መስፈርቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ። ይህም ለኬሚካል ጥቅም ላይ የመዋል የእድሜ ደረጃች ላይ ይተገበራል ለምሳሌ ጥቅም ላይ ማዋል፣ ክምችት እና የኬሚካል ጉዞ። ከኬሚካል የሚወጣ የቆሻሻ ቁጥጥር እንደ ጎጂ ቆሻሻ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በዚህ መመሪያ ሽፋን አያገኝም።

# 2 ፍቺዎች

“ኬሚካል አያያዝ” የኬሚካሎች አጠቃቀም፣ አከመቻቸት እና መጓጓዝን ያካትታል።

“አካባቢያዊ የደህንነት መመርያ” ከደህንነት መረጃ ሉህ እና ከአከባቢ ሁኔታዎች መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ በአከባቢው የተሰራ የደህንነት መመሪያ ማለት ነው።

“የደህንነት መረጃ ሉህ” ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ከሚወሰዱ የተወሰኑ የኬሚካል እና የደህንነት ጥንቃቄዎች ጋር ስለሚዛመዱ አደጋዎች ለንግድ ተጠቃሚዎች የአምራች መረጃ ማለት ነው። እንደ አካባቢው ደንብ የደህንነት መረጃ ሉሁ (SDS) ትክክለኛ ቅርጸት ሊለያይ ይችላል።

# 3 ሃላፊነቶች

## 3.1 አስተዳዳሪዎች/ሃላፊነት ያለበት ሰው

ተሳታፊው አስተዳዳሪ/ሃላፊነት ያለበት ሰው ሊያረጋግጥ የሚገባቸው ነገሮች፡

- ከኬሚካሎች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች በተገቢው የሰለጠኑ እና አግባብነት ያላቸውን የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) የሚጠቀሙ መሆኑን፣
- የተወሰኑ ኬሚካሎችን በመጠቀም ሊባባሱ በሚችሉ የታወቁ የሕክምና ሁኔታዎች የሚታመሙ ተቀጣሪዎች እንደዚህ ያሉ ኬሚካሎችን ካለበት የስራ ተግባር እንዲገለሉ መደረጉን ፣ እና
- እርጉዝ ተቀጣሪዎች ለኬሚካል አለመጋለጣቸውን ያረጋግጣሉ።

## 3.2 ኬሚካል የሚይዙ ግለሰቦች

ተቀጣሪዎች በኬሚካሎች ተጽዕኖ ሊያድርባቸው ስለሚችሉ የጤና ሁኔታዎች (ወይም እርግዝና) ለቀጣሪዎቻቸው ማሳወቅ አለባቸው ።

ኬሚካሎችን የሚይዝ ማንኛውም ሰው በደህንነት መረጃ ሉህ ሲደነገግ እና በተጋላጭነት ትንተና እንደ ማቃለያ እርምጃ ተብሎ ሲገለጽ ተገቢውን PPE መጠቀም አለበት ።

# 4 መስፈርቶች

## 4.1 ጠቅላላ መስፈርቶች

የሚከተሉት መስፈርቶች የሚተገበሩ ይሆናል፡

- የስራ ቦታ የኬሚካል አስተዳዳሪ የሚሾም ሲሆን እና የሚከተሉት ሃላፊነቶች አሉበት፡
  - የኬሚካል ማከማቻ ቦታ መቆጣጠር፣
  - የኬሚካል መዝገብ መጠበቅ፣
  - መደበኛ ምርመራዎችን ማካሄድ እና
  - የኬሚካል ተጠቃሚዎችን ማሰልጠን።

- ኬሚካል ጥቅም ላይ ስይውል በፊት እንደ የአከባቢው የተጋላጭነት ግምገማ፣ የተጋላጭነት ቅነሳ/የህክምና ዕቅድ መፍጠር እና አግባብነት ያላቸው የቁጥጥር እርምጃዎች መተግበር አለባቸው።

- የንጥረ ነገር ገደቦች መከተል አለባቸው፡ የኤሪክሰን የተከለከሉ እና የታገዱ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር።

- ከኬሚካሎች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች በተገቢው የሰለጠኑ እና አግባብነት ያላቸውን የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) የሚጠቀሙ መሆን አለባቸው።

- በጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎች በሙሉ

- ሊዘረዘሩ፣
- በክትትል እና ቁጥጥር ስር ሊሆኑ (የት በጥቅም ላይ እንደሚውሉ ጨምሮ)፣
- ባልተጎዱ፣ ምልክት በተደረገባቸው እና ምቹ የትሽጉ መያዣዎች ሊቀመጡ እና
- ተግባራዊ በሚሆን ህግ እና የደህንነት መረጃ ሉሁ ጋር በተዘመደ መልኩ ሊቀመጡ፣ ጥቅም ላይ ሊውሉ እና ሊጣሉ ይገባል።

የኬሚካሎች መዝገቦች በተጠየቀ ሰዕት መቅረብ መቻል አለባቸው።

## 4.2 የደህንነት መረጃ ሉህ

"የደህንነት መረጃ ሉህ" ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ከሚወሰዱ የተወሰኑ የኬሚካል እና የደህንነት ጥንቃቄዎች ጋር ስለሚዛመዱ አደጋዎች ለንግድ ተጠቃሚዎች የአምራች መረጃ ማለት ነው። እንደ አካባቢው ደንቦች የደህንነት መረጃ ሉሁ ትክክለኛ ቅርጸት ሊለያይ ይችላል።

የኬሚካሎች ተጠቃሚዎች በደህንነት መረጃ ሉሆች ውስጥ ያሉትን መረጃዎች እና መመሪያዎች መከተል አለባቸው ።

SDS በትንሹ ስለ እያንዳንዱ ኬሚካል ባህሪዎች፣ አካላዊ, ጤና እና አካባቢያዊ አደጋዎች፣ የመከላከያ እርምጃዎች፣ ኬሚካሉን ለመያዝ፣ ለማከማቸትና ለማጓጓዝ የጥንቃቄ እርምጃዎች መረጃ ሊያካትት ይገባል።

የደህንነት መረጃ ሊሆች:

- በአከባቢው ቋንቋ፣
- ኬሚካሎቹ በጥቅም ላይ ሲውሉ እና ሲከማቹ በቀላሉ የሚገኙ፣
- ድንገተኛ አደጋ የሚከሰት እንደሆነ እንደ 2ተኛ ስብስብ በቀላሉ የሚገኙ እና
- ጊዜውን የጠበቁ መሆን አለባቸው።

## 4.3 ምልክት ማድረግ እና መለጠፍ

ወደ ትናንሽ መያዣዎች ሲዘዋወሩ ጨምሮም ኬሚካሎች ሁል ጊዜ በኬሚካሉ ስም እና የአደገኛ ምልክቶች በትክክል በትክክል ምልክት የተደረገባቸው እና የተለጠፉ መሆን አለባቸው።

## 4.4 ተቀጣጣይ እና/ወይም ፈንጂ እቃዎች

አደገኛ ፣ ተቀጣጣይ እና / ወይም ፈንጂ ቁሳቁሶችን አያያዝ የሚከናወነው ከ የእሳት አደጋ መከላከያ ጋር በተዘመደ መልኩ አጠቃላይ የአካባቢን ተጋላጭነት ግምገማ እና የቁጥጥር እርምጃዎች አፈፃፀም ተከትሎ ብቻ ነው።

# 5 የህክምና አቋም እና ምላሽ

የተቀጣሪ የጤና ሁኔታ በህግ በተፈቀደበት ጊዜ የአከባቢው የተጋላጭነት ግምገማ አካል መሆን አለበት።

ተቀጣሪዎች በስራ ላይ ሳሉ በራሳቸው ወይም በተቀጣሪ ባልደረባቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ አካላዊ ወይም ሌላ ህመሞችን ለቀጣሪዎቻቸው ማሳወቅ አለባቸው ። አንድ ተቀጣሪ የተወሰኑ ኬሚካሎችን በመጠቀም ሊብስበት የሚችሉ የታወቁ የሕክምና ሁኔታዎች የሚታመም ከሆነ ለቀጥታ አስተዳዳሪው ማሳወቅ አለበት።

## 6 የተጋላጭነት ግምገማ እና እቅድ

የኬሚካሉ ጥቅም ላይ መዋል አካባቢው የተጋላጭነት ግምገማ ከመጀመሪያው ጥቅም በፊት መደረግ አለበት። እንዲህ ዓይነቱ ግምገማ የስልጠና አስፈላጊነትን ግምገማ ፣ የተቀጣሪውን የጤና ሁኔታ (በተፈቀደው ቦታ) ፣ የPPE አስፈላጊነት ፣ በደህንነት መረጃ ሉህ ውስጥ የተጠቀሱትን ጨምሮ ሌሎች የቁጥጥር እርምጃዎችን እና ሌሎች ዝቅተኛ አደገኝነት ያላቸውን ተተኪዎችን መጠቀምን ያካትታል

የአከባቢው የተጋላጭነት ግምገማ የጥቅም ሁኔታዎች ለውጥ ካለ ሊደገም ይገባል። ይህም የሰዎች ለውጥ ፣ አዲስ የአደጋ መረጃ ፣ በአጠቃቀም መጨመር ወይም በሌሎች በስራ ሂደት ወይም በአከባቢው ላይ ወሳኝ ለውጦች የሚመጣ ተጨማሪ መጋለጥ ሊሆን ይችላል።

## 7 ክትትል እና ግምገማ

ወደ አነስተኛ አደገኝነት ያላቸው አማራጮች የመተካት አዋጭነትን ለመገምገም በየአመቱ የኬሚካል አጠቃቀም ግምገማ ይደረጋል።

ለዚህ መስፈርት ተገዢነት የሚከተሉትን መዝገብ በመያዝ በክትትል ስር የሚሆን እና የሚገመገም ይሆናል፡

- የክስተት ስታትስቲክስ፣
- በየትኛውም የስራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውል የኬሚካል ብዛት እና አይነት፣ እና
- በየአንዳንዱ ተቀጣሪ እና ኬሚካል ስልጠና

## 8 ማጣቀሻዎች

[የኤሪክሰን የተከለከሉ እና የታገዱ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር።]

## 9 የለውጥ መረጃ

ካለፈው ክለሳ ጀምሮ የለውጦች አጭር መግለጫ፡

1 መግቢያ ዘምኗል

2 የፍቺዎች አንቀፆች እና ሃላፊነቶች ተጨምረዋል

3 የስራ ቦታ የኬሚካል አስተዳዳሪ እና ሃላፊነቶች ወደ መስፈርቶች ተጨምረዋል

4 የደህንነት መረጃ ሉህ አንቀጽ ተብራርቷል

5 የህክምና አቋም እና ምላሽ ተጨምሯል